# ጾም በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት

ጾም ከተወሰኑ ምግቦች ለተወሰኑ ሰዓታት መከልከል ነው ። አንዳንድ ጊዜም ከማንኛውም የምግብ አይነት ለተወሰኑ ሰዓታት በመከልከል የሚሆን ጾም አለ ።

ጾም ከጥንት ዘመን ጀምሮ በሃይማኖታውያን ና ከሃይማኖት ውጭ በሆኑ ሕዝቦች ዘንድ የተለመደ ነበር ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ጾም በብዙ የተለያዩ ምክንያቶች የጾም እንደነበር በየአንቀጹ ተጽፎ ይገኛል ። ለምሳሌ ከእግዚአብሔር ጋር በራእይና በሕልም ወይም በመልአክ ለመነጋገር ለመንፈሳዊ ተልእኮ ለመዘጋጀት ከእግዚአብሔርም አንድ ነገር ለማግኘት የጾሙ ሰዎች ነበሩ ።

በዚህ መሠረት ሙሴ ዐሥሩ ት[illegible]ትን ከመቀበሉ በፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደ ጾመ በዘጸአት 34፡ 28 ተጽፎአል ነቢዩ ኤልያስም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንደ ጾመ ከእግዚአብሔር ድምጽ ሰምቶአል ። 1 ነገሥ 19 ፡ 8 ።

ማንኛውም እስራኤላዊ አንድ አስጨናቂ ነገር ሲገጥመው እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያሳዝን ድርጊት ሲፈጽም በግል መጾም የተለመደ ነበር ። ይህም የንስሐ ጾም ይባላል ። ዳዊትና አክአብ በየዘመናቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በተላለፉ ጊዜ ማቅ ለብሰው ትቢያ ነስንሰው ጾመዋል ። 2 ሳሙ 12 ፡ 16 - 23 ።።

1 ነገሥ . 21 ፡ 27 ።

በሀገር ላይ ከባድ አደጋ ጦርነትና መቅሠፍት ሲደርሱ በአዝመራ ላይ አንበጣና ተምች ሲወርዱ በሰውና በእንስሳ ላይ አባርና ቸነፈር ሲነሡ የማሕበር ጾም ይደረግ እንደነበር የሚከተሉት ጥቅሶች ያመለክታሉ ። ለምሳሌ የእስራኤል ልጆች በጊብዓ ላይ በብንያም ልጆች ድል በተመቱ ጊዜ በማኅበር ሆነው ከጡዋት እስከማታ ጾመዋል። መሳፍ.20፡26።የሞአብና የዓሞን ልጆች በዮሳፍጥ ላይ በኃይል ስለተነሱ ንጉሡ ዮሳፍጥ በይሁዳ ሁሉ ጾምን አወጀ። 2 ዜና 20 ፡ 3 ። ሐማ የተባለው ጨካኝ ሰው በፋርስ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ እንዲጠፉ በመከረ ጊዜ በአስቴር ትእዛዝ አይሁድ ሁሉ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ምንም ሳይቀምሱ ጾመዋል። አስቴ . 4፡ 16 ፡ የነነዌ ሰዎችም ይህን የመሰለ ተግባር ፈጽመዋል ዮናስ. 3፡4 -10 ።

በትንቢተ ኢዮኤል አንድና ሁለት ምዕራፎች ላይ እንደተገለጠው ሀገሩን ሁሉ አንበጣ በመውረሩ የዓዋጅ ጾም ተደርጎ ነበር ።

የእስራኤል ልጆች ከምርኮ በተመለሱ ጊዜ የመከራ ቀኖችን በየዓመቱ በጾም ያስታውሱ እንደነበር ዘካርያስ ይናገራል። ዘካ 7 . 5 ። ከዚህም ጋር እስራኤላውያን ኃጢአታቸውን ለማስታወስ የሚያደርጉት የኑዛዜ ጾም በመጽሐፈ ነህምያ ተመዝግቦአል ። ነህም . 9፡ 1።

ሰው በሞተ ጊዜ ጾም መጾም በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነበር ። ይህም ሰውየው ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚቀበርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ከሞተም በኋላ ከአንድ ቀን እስከ ሰባት ቀናት የሚጾም ነው ። 1 ሳሙ . 31 ፡ 13 ። 2 ሳሙ 1 ፡ 12። እግዚአብሔር አምላክ ለእስራኤላውያን በሰጣቸው ሥርዐተ በዓል በሰባተኛው ወር በዐሥረኛው ቀን የማስተማሪያ ቀን ነበር በዚህም ቀን የእስራኤል ልጆች ሁሉ ሰውነታቸውን እንዲያስጨንቁ ታዝዘዋል ዘሌ 23 ፡ 27 - 32 ። ሰውነትን ማስጨነቅ ማለትም በጾም ነው ። ከዚህም የተነሣ ጾም ሥጋን ማስጨነቅና ማድከም ለነባቢት ነፍስም ማስገዛት ነው ተብሎ ተተርጉሞአል ።

የጾም ቀናት በብሉይ ኪዳን ለአንድ ለሶስት ለሰባትና ለአርባ ቀናት እንደ ነበሩ እላይ በተዘረዘሩት ታሪኮች መረዳት ይቻላል ነገር ግን ከአንድ ቀን በታች ከአርባ ቀናትም በላይ የሆነ የጾም ጊዜ መኖሩ በብሉይ አልተጠቀሰም ። ጊዜያቱም አንዳንድ ጊዜ ለ 12 ሰዓታት ያህል ሲሆን በሌላ ጊዜ ደግሞ ለ72 ሰዓታትም የሚጾም ጾም ነበር አስቴ . 4 . 16። ከዚህ በላይ የሆነው የጾም ሰዓት ግን በተአምራዊ እንጂ በሥጋዊ ኃይል እንደሆነ መገመት ያስቸግራል ።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች እውነተኛ ና ልባዊ የሆነ የጾም ሥርዐት አይታይም ነበር ። ስለዚህም ነቢያት ሁኔ ብዝነት ይደረግ የነበረውን ጾም ተቃውመዋል ። ገሥጸዋልም ኢሳ. 58 ፡ 3 - 7። ኤር . 14 ፡ 12 ።

## በሐዲስ ኪዳን

መድኃኒታችን ክርስቶስ የፈሪሳውያንን ከንቱ ውዳሴ ነቀፈ እንጂ ጾምን አልተቃወመም ። ጾም የትሕትና ራስን ለእግዚአብሔር የማስገዛት ምልክት ስለሆነ በስውር እንጂ በዓዋጅ መሆን እንዳይገባው ጌታችን አስተማረ ። ማቴ 6 . 16 - 18 ።

በጌታችን ጊዜ የነበሩት አይሁድ በሳምንት ሁለት ቀናት ሰኞንና ሐሙስን ይጾሙ ነበር ሉቃ 18 ፡ 12 የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርትም አብዝተው ይጾሙ እንደነበር በማቴዎስ ወንጌል 9፡ 14 - 17 ተገልጦአል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾመ ማቴ 4 ፡ 2 ። ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ እርሱ በነበረበት ዘመን በየዓመቱ ይህን ጾም እንዲጾሙ አላዘዛቸውም እንዲያውም ደቀ መዛሙርቱ ለምን እንደማይጾሙ ተጠይቆ የሚከተለውን መልስ ሰጠ ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሠርገኞች ሊጾሙ አይችሉም ። ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ በሚለይበት ጊዜ ይጾማሉ ። ማር 2 ፡ 18 - 22

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን በማለቱ ሐዋርያት የፈሪሳውያንን ጾም አይነት እንዳይጾሙ መከልከሉን ያስረዳል። ሙሽራው በሚለይበት ጊዜ እንደሚጾሙ ይህም በሐዋርያት ዘመን



www.ethiopianorthodox.org

የጌታ የሞቱ መታሰቢያ ሆኖ በየዓመቱ ለሁለት ቀናት ይጾሙ ነበር ። ዛሬም የአክፍሎት ጾም እየተባለ በየዓመቱ ይጾማል።

በሐዋርያት ዘመን ስለ ጾም ቀዋሚ ሕግ አልነበረም ስለዚህም እስከ ሁለተኛው መቶ ዓመት ጾም የግል ፈቃድ ነበር ምእመናኑ አብዝተው ሆነ አሳንሰው ለመጾም ነፃነት ነበራቸው ።

ሐዋርያትም መዓረገ ክሕህነትን ከመቀበል በፊት ጾም እንደሚገባ በተግባር አሳይተዋል ።

ለምሳሌ ጳውሎስና ባርናባስ በመንፈስ ቅዱስ ተጠርተው ሥልጣነ ክህነትን ከመቀበላቸው በፊት ጾመዋል ። ግን ለምን ያህል ቀን እንደ ጾሙ አልተገለጠም ። የሐዋ . 13 ፡2 ። 14 ፡ 23

በመሠረቱ የሐዲስ ኪዳን ጾም ስለ ክርስቶስ ፍቅር የተደነገገ ነው ። በየሳምንቱ የሚጾሙት ዐርብና ረቡዕ ክርስቶስ በፍቅሩ ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ ለማስታወስ ነው ። ዐርብ ጌታችን ኢየሱስ የሞተበት በሞቱም ድኅነተ ዓለም የተፈጸመበት ስለሆነ ይጾማል ረቡዕም እንዲሰቀልና እንዲሞት የተወሰነበት በመሆኑ እንዲጾም በሐዋርያት ተደንጎአል ። ዲስቅ . 7፡ 4

ከዚህም ሌላ በጥንት ጊዜ ክርስቲያኖች አንድ አይነት ፈተና ሲገጥማቸው ምህላና ጸሎት ይዘው ለተወሰኑ ቀናት ይጾሙ ነበር ። እንደዚሁም ንስሐ ሲገቡ ካህኑ ብፈቀደላቸው መሠረት ይጾሙ እንደነበር የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል ዛሬም ይህ አይነት ጾም ይሠራበታል ።

ከጥምቀትና ከቁርባን በፊት ሰውነትን ለማንጻት ማንኛውም ክርስቲያን መጾም እንደሚገባው ሐዋርያት አስተምረዋል በኋላም በአራተኛው ምእት ዓመት በትልቁ ባስልዮስና በዮሐንስ አፈወርቅ ዘመን ከቁርባን በፊት ጾም ተሠርቷል ።

ከዚህም የተነሣ ከታላላቅ በዓላት በፊት በዋዜማው ስለ በዓሉና ስለ ቅዱስ ቁርባን ክብር መጾም ተጀመረ ። ይልቁንም ከትንሣኤ በፊት ለአንድ ሳምንት ያህል በየዓመቱ እንዲጾሙም የታወጀው በዚሁ በአራተኛው ምእት ዓመት ነው ። ይህም ሳምንት ቅዱስ ሳምንት ወይም ሰሙነ ሕማማት እየተባለ ይጠራ ጀመረ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 40 ቀንና 40 ሌሊት የጾመውን ጾም በአራተኛው ምእት ዓመት እንዲጾም ተወሰነ ነገር ግን እንደዛሬው ለሰባት ሳምንታት ሳይሆን ለሁለት አንዳንዴም ለሶስት ሳምንታት ብቻ ይጾም ነበር ።

ከመጀመሪያው ምእት ዓመት እስከ ሶስተኛው ዘመን ድረስ በጾም ቀን ዳቦ ውሃና ጨው ይፈቀድ ነበር ። በኋላ ግን ፍራፍሬና አታክልት ይበላ ጀመር ። እየቆዩም አንዳንዶቹ ዕንቁላልና ቅቤው የወጣ ለት ወተት ይጠቀሙ እንደነበር ይነገራል ። ዛሬ ግን ዕንቁላልና ጥሉላት አልኮል ነክ መጠጥም እንዲወስዱ ቤተ ክርስቲያን አትፈቅድም ።

ለማጠቃለል ያህል በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት የጾም ጥቅም መንፈሳውያን ነገሮችን ለማሳወቅና ሕይወትን ለማደስ ነው። እውነተኛ ክርስቲያን ከዝሙትና ከሥጋዊ ደስታ ርቆ በመጾም በመመጽወትና በመጸለይ እግዚአብሔርን ያገለግላል ጾም ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ያገናኛል ። ሕይወትን ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃ ያደርሳል ። ጾም ሥጋን ለነፍስ ያስገዛል ። ከኃጢአትና ከስህተት በመከልከል የሚሆን ጾም ሕወትን ወደ እውነተኛ መንገድ ይመራል።

✓ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

Tinsae Magazine, No.53, Yekatit 1974

www.ethiopianorthodox.org